# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

# SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

| | | |
|---|---|---|
| 3ki Diro Kiiro 28<br><br>Hawaasa, Badheessa 12/2015 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፫ኛ ዓመት ቁጥር ፳፰<br><br>ሀዋሳ፣ መጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም |



**Amado**

**Lallawu Kiiro 28/2015**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Latishshu Uurrinshubba Lallawa Qoola….**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፳፰/፳፻፲፭**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ…… ገጽ**


## Lallawu Kiiro 28/2015

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Latishshu Uurrinshubba Lallawa

Qoqqowu mootimma miinju handaarubba giddo dikkote anje kalaqqanno foonqe xiinxallotenni badatenni latishshu uurrinshubba uurritannonna massagantanno seeru hanqafo diriirsatenni qoqqowu giddo taalcho miinju lopho heedhanno gede assa hasiissannota ikkite leeltinnohura;

Latishshu uurinshubba hewisamaano, lifixa, gumaammanna tirfaamma ikkite miinju lopho buuxissanno ha’rinsho giddo hasiisanno qeecha fula

## አዋጅ ቁጥር ፳፰/፳፻፲፭

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ

የክልሉ መንግሥት በኢኮኖሚው ዘርፎች ውስጥ የገበያ እጥረት የሚፈጥረውን ክፍተት በጥናት በመለየት የልማት ድርጅቶች የሚቋቋሙበትና የሚመሩበት የሕግ ማዕቀፍ በመዘርጋት በክልሉ የተመጣጠነ የኢኮኖሚ እድገት እንድኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የልማት ድርጅቶች ተወዳዳሪ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ትርፋማ በመሆን የኢኮኖሚ ዕድገትን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና መወጣት እንዲችሉ ተቋማዊ አደረጃጀታቸዉ የአስተዳደር

dandiissitanno uurrinshaame tantanonsa gashshootaame wolapho kaima assi’rinnoha ikke mootimmatenna dagate horo agarsiisate qorqorsha, irkonna harunso assinanni xawo loosu amuraate diriirsa hasiissannota ikkitinnohura;

Miinju handaarubbara assinanni millimmonni mootimma dagate latishshira irkissannota ledote eo afi’rate dandiitannonna garunni gamba assitanno injo kalaqa hasiissinohura;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri Quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) aana uynoonnisi biilloonyi garinni aaninoha lallawino.

**GAFA MITE**

**<u>XAPHOOMA WORO</u>**

1. **Harancho Umo**

   Konne lallawa **“Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Latishshu Uurrinshubba Lallawi Kiiro 28/2015’’** yine xawisa dandiinanni.

2. **Tiro**

   Konni Lallawi giddo qaalu eo wole tiro uyisiissannota ikka hoogguro:-

   1. **“Qoqqowo’’** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
   2. **“Mootimma”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmaati.
   3. **“Jefisiisaano Bissa Amaale Mine”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma jefisiisaanote bissa Amaale mineeti.

ነጻነትን መሠረት ያደረገ ሆኖ የመንግሥትና የህዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ ቁጥጥር የሚደረጉበት፤ የሚከታተሉበት እና የሚደገፉበትን ግልጽ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢኮኖሚው ዘርፎች በሚደረግ እንቅስቃሴ መንግሥት ለህብረተሰብ ልማት የሚረዳዉን ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ለማግኘት የሚችልበትን እና በአግባቡ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፤

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ (ሀ) ላይ በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት የሚከተለዉን አዉጇል፡፡

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>**

1. **አጭር ርዕስ**

   **ይህ አዋጅ “የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፰/፳፻፲፭” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡**

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡
   2. **“መንግሥት”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡
   3. **“የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት ነው፡፡
   4. **“ባለስልጣን”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንግስት የልማት ድርጅቶች

4. **“Biilloonye”** yaa Qoqqowu Moottimmate Latishshu Uurrinshubba Qorqorshi Biilloonyeeti.

5. **“Boorde”** yaa latishshu uurrinsha looso aliidimatenni massaganno gede uurrisate wodho garinni uurritanno latishshu uurrinsha boordeeti.

6. **“Latishshu Uurrinshubba”** yaa wo’munni wo’ma woy gamunni mootimmate kaapitaalenni, konni Lallawi garinni uurrisate Wodhonni uurrite horo afi’rate yite laashshate, beehate, ijaarsatenna owaante aate looso woy woloota ikonoometenna daddalu loossa ledo amadantinno loossa aana bobbakkino uurrinshubbaati.

7. **“Dagoomitte Owaante Aate Gadacho”** yaa latishshu uurrinshubba loosi dagoomunna qooxeessu aana hee’rannosi hekko hedote giddo woratenni konne Lallawanna wolootta garimma noonsa seerubba kaima assatenni wolqansanninna womaashshinsanni dagate owaante aate gadachooti.

8. **“Damatte Hanqafaancho”** yaa latishshu uurrinshubba lainohunni biilloonyu qixxeessanno boordete miilla loosu waagi baatooshshe, loosu ha’risaano horote bikka, loosaasinete barru hoshshonna horo, loosatenna galtinote amuraateeti.

9. **“Kaimu Kaapitaale”** yaa mitte latishshu uurrinsha uurritanno yannara womaashshunni woy womaashshunninna

ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፡፡

5. **“ቦርድ”** ማለት የልማት ድርጅቶችን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት እንድመራ በመቋቋሚያ ደንብ መሠረት የሚቋቋም የልማት ድርጅት ቦርድ ነው፡፡

6. **“የልማት ድርጅቶች”** ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት ካፒታል፣ በዚህ አዋጅ መሠረት በመቋቋሚያ ደንብ በመቋቋም ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የማምረት፣ የማከፋፈል፣ የግንባታና አገልግሎት የመስጠት ተግባር ወይም ሌሎች ከኢኮኖሚና ንግድ ተግባራት ጋር በተያያዙ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች ናቸዉ፡፡

7. **“የማህበራዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ”** ማለት የልማት ድርጅቶች ሥራ በማህበረሰቡ እና በአከባቢዉ ላይ የሚኖረዉን ተጽእኖ ግምት ዉስጥ በማስገባት ይህን አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎችን መሠረት በማድረግ በጉልበታቸው እና በገንዘባቸው ለማህበረሰቡ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ነው፡፡

8. **“መሠረታዊ ማዕቀፍ”** ማለት የልማት ድርጅቶችን በተመለከተ በባለስልጣኑ የሚዘጋጅ የቦርድ አባላት የሥራ ዋጋ ክፍያ፣ የስራ አስኪያጆች የጥቅም ገደብ፣የሠራተኞች አበልና ጥቅማ ጥቅም፣ የአሰራር እና የመተዳደሪያ ሥርዓት ነው፡፡

9. **“መነሻ ካፒታል”** ማለት አንድ የልማት ድርጅት በሚቋቋምበት ጊዜ በገንዘብ ወይም በገንዘብ እና በዓይነት የሚመደብለት ሀብት ነው፡፡

10. **“ካፒታል”** ማለት አንድ የልማት ድርጅት

uduunnichunni gaammanni jirooti.

10. **“Kaapitaale”** yaa mitte latishshu uurrinsha uurritanno yannaranna hakkuy gedensaanni mootimmatenni gaammanni xaphooma buuxantino jiro gaammoonni yannara noose waagaati.

11. **“Xaphooma Buuxantino Jiro”** yaa xaphoomu jironni harancho yanna asale, seeda yanna asalenna wooloota asalubba xeinseenna afantanno jirooti.

12. **“Xaphooma Jiro”** yaa baalanka milli yaannokkinna milli yaanno jajja, gamba assinanni jiro, kiirranni womaashsha, baankete shallago, latishshu uurrinshubba bisi-afiriweelo jiro, owaantete baatooshshubbanna woloota asalubba xaphisanno.

13. **“Buuxamino Tirfe”** yaa baajeetete diri giddo eote womaashshinna wolootu addi addi batooshshubbanni afantanno addi addi fulo, looso ha’risate, damoozaho, seeru garinni fulo assinoonni shallagubba, akkallete xeishsha hattono qallonna taakise baanteenna gattanno shallagooti.

14. **“Mootimmate Tirfi Qeecha”** yaa buuxamino tirfinni seeru rizerve shallago xeinseenna mootimmate gatanno qeechaati.

15. **“Mancho”** yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannihimmate qoosso uynoonnisi bisooti.

16. **“Odiitere”** yaa konni Lallawi garinni uurritino latishshu uurrinshubba jiro qorqoranno kalaqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso uynoonnisi bisooti.

17. Konni Lallawi giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonnihu wole koo-teemmano hanqafanno.

**3. Jeefishshu Mami-geeshsha**

በሚመሠረትበት ጊዜና ከዚያ በኋላ በመንግሥት የሚመደብለት ጠቅላላ የተጣራ ሀብት በተመደበበት ጊዜ ያለው ዋጋ ነው፡፡

11. **“ጠቅላላ የተጣራ ሀብት”** ማለት ከጠቅላላ ሀብት የአጭር ግዜ ዕዳዎች፣ የረጅም ግዜ ዕዳዎች እና ሌሎች ዕዳዎች ተቀንሶ የሚገኝ ሀብት ነዉ፡፡

12. **“ጠቅላላ ሀብት”** ማለት ሁሉም የማይንቀሳቀስና የሚንቀሳቀስ ንብረት፣ ተሰብሳቢ ሀብት፣ ጥሬ ገንዘብ፣ የባንክ ሂሳብ፣ የልማት ድርጅቶች የማይዳሰሱ ሀብቶች፣ የአገልግሎት ክፍያዎች እና ሌሎች እዳዎችን ያጠቃልላል፡፡

13. **“የተጣራ ትርፍ”** ማለት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከገቢ ገንዘብና ከሌሎች ልዩ ልዩ ክፍያዎች ከሚገኙት ልዩ ልዩ ወጪዎች፣ ለሥራ ማስኬጃ፣ ደመወዝ፣ በሕጉ መሠረት ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች፣ የእርጅና ቅናሽ ግምት እንዲሁም ወለድና ታክስ ተከፍሎ የሚቀረው ሂሳብ ነው፡፡

14. **“የመንግስት የትርፍ ድርሻ”** ማለት ከተጣራ ትርፍ ህጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳብ ተቀንሶ ለመንግሥት የሚቀር ድርሻ ነው፡፡

15. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

16. **“ኦዲተር”** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚቋቋሙ የልማት ድርጅቶችን ሀብት የሚመረምር የተፈጥሮ ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

17. በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛዉንም ጾታ ያካትታል፡፡

Kuni Lallawi latishshu uurrinshubba aana jeefamannoha ikkanno.

## GAFA LAME

## <u>LATISHSHU UURRINSHUBBA UURRA, SEERU MANNIIMMA, HUNDAANCHIMMANNA TANTANO</u>

**4. Latishshu Uurrinshubba Uurrate Balaxi-ikkitubba**

1. Ayee latishshu uurrinsha uurrate albaanni aantete noo balaxi-ikkitubba wonsha hasiissannose:
   a) Uurrinsha uurrisate dikkote foonqe noota leellishshanno xiinxallo ha'risa;
   b) Kaimaho baantoonni kaapitaale wommaashshi uurritanno latishshu uurrinsha su'minni fannoonni baankete akkaawuntera eo assa;
   c) Uduunnichunni assinoonni baatooshshi ogeessunni gammataminoha woy odiitere buuxxino shallago noosiha ikkasinna shallagote mazigawi garinni jeefisamasi;
   d) Uduunnichunni assinoonni baatooshshi jajju gimmite tittirshu xawishshi rippoorte; mittu mittunku jajjira uynoonni waaginna gimmite ha'rinsoonni hayyo hee'ra;
2. Konni Quwi cinaanchu quwi (1) (b) xawinsoonni womaashshi uurrisate wodho wonsina geeshsha cufo baankete akkaawuntera ofollanno.
3. Biilloonyu latishshu uurrinsha uurrisate

**3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የልማት ድርጅቶች መቋቋም፣ የሕግ ሰውነት፣ ተጠሪነት እና አደረጃጀት</u>

**4. የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም ቅድመ- ሁኔታዎች**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለበት፡-
   ሀ) ለድርጅቱ መቋቋም የገበያ ክፍተት መኖሩን የሚያሳይ ጥናት መኖሩ፤
   ለ) ለመነሻ የተከፈለው የካፒታል ጥሬ ገንዘብ በሚቋቋመው ድርጅት ስም በተከፈተ ባንክ ገቢ መሆኑ፤
   ሐ) በአይነት የተደረገ ክፍያ በባለሙያ የተገመተ ወይም በኦዲተር የተረጋገጠ ሂሳብ ያለው መሆኑንና በሂሳብ መዝገቡ መሠረት መፈጸሙን፤
   መ) በአይነት የተፈጸመው ክፍያ የንብረት ግምት ዝርዝር መግለጫ ሪፖርት፤ ለእያንዳንዱ ሀብት የተሰጠውን ዋጋ እና ግምቱ የተካሄደበት ስልት ያለው መሆኑን፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ለ) የተመለከተዉ ገንዘብ የድርጅቱ መቋቋሚያ ደንብ እስከሚጸድቅ ድረስ በዝግ የባንክ ሂሳብ ይቀመጣል፡፡

fushshino fulo heedhuronna odiiterootunni buuxantinnoha ikkiro uurrinshate kaapitalera kiirantanno;

**5. Latishshu Uurrinshubba Uurrisare**

1. Ayee latishshu uurrinsha konni Lallawi garinni uurrisate wodhonni qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini uurrisanno.
2. Qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini hasiishshisi garinni quchumu gashshootinni galtannonna dagate owaante uytanno latishshu uurrinshubba uurrisa dandaanno.

**6. Latishshu Uurrinshubba Uurrisate Wodho Amado**

Latishshu uurrinshubba uurrisate wodho ajay ajeenna aantete noo amado heedhasera hasiissanno:

1. Uurrinshate su'ma;
2. Uurrinshate hexxo;
3. Uurrinshate biilloonyenna loosu qeecha xawisanno tittirshu xawishsha;
4. Uurrinsha konni Lallawinni galtannota ikkase;
5. Fajjinoonni kaapitaale;
6. Uduunnichunninna womaashshunni baantoonni kaimu kaapitaale;
7. Uurrinshate qaru loosu mini teesso;
8. Uurrinshate sinu loosu minna heedhasera dandiitanotanna
9. Uurrinsha keeshshitanno yanna.

**7. Latishshu Uurrinshubba Seeru Mannihimma**

Ayee latishshu uurrinshara seeru mannimma heedhannose.

**8. Hundaanchimma**

Latishshu uurrinshubba hundaanchimma biilloonyeho ikkitanno

3. ባለሥልጣኑ ለድርጅቱ ምስረታ ያደረገዉ ወጭ ካለና ይህም በኦዲቴሮች የተረጋገጠ ከሆነ ለድርጅቱ በካፒታልነት ይታሰባል፡፡

**5. የልማት ድርጅቶች ስለማቋቋም**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት በመቋቋሚያ ደንብ በክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡
2. የክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ በከተማ አስተዳደር የሚተዳደሩና ለህብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ የልማት ድርጅቶችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

**6. የልማት ድርጅቶች የመቋቋሚያ ደንብ ይዘት**

የልማት ድርጅቶች መቋቋሚያ ደንብ ቢያንስ የሚከተሉት ይዘቶች ሊኖሩት ይገባል፡-

1. የድርጅቱ ስም፤
2. የድርጅቱ ዓላማ፤
3. የድርጅቱን ሥልጣንና ተግባር የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ፤
4. ድርጅቱ በዚህ አዋጅ የሚተዳደር መሆኑ፤
5. የተፈቀደው ካፒታል፤
6. በዓይነት እና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ መነሻ ካፒታል፤
7. የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፤
8. ድርጅቱ ቅርንጫፎች ሊኖሩት እንደሚችል፤ እና
9. የድርጅቱ የቆይታ ጊዜ፡፡

**7. የልማት ድርጅቶች የሕግ ሰውነት**

ማንኛውም የልማት ድርጅት የሕግ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

**8. ተጠሪነት**

የልማት ድርጅቶች ተጠሪነት ለባለስልጣኑ

**9. Xa’mamooshshe**

Latishshu uurrinsha asale baata dandiitannohu uurrinsha noose jironni calla ikkanno.

**10. Latishshu Uurrinshubba Loosu Amuraate**

1. Ayee latishshu uurrinsha dikkote giddo heewisamaancho ikkite loossannoha ikkanno.
2. Konni Quwira cinaancho quwa (1) aana worroonniri noo gedeenni hee’reenna dagate horo agarsiisate hasiissannoha ikke leelliro mootimma latishshu uurrinshubba dhaaddote loosiissara dandiitanno.

**11. Latishshu Uurrinsha Tantano**

Ayee latishshu uurrinsha:-

1. Boorde
2. Qara loosu ha’risaanchinna hasiishshisi garinni layinki loosu ha’risaanchi;
3. Wolootu loosoho hasiissanno loosaasiine heedhannose.

**12. Latishshu Uurrinshubba Boorde.**

1. Boordete miilla filantannohunna gaamantannohu noonsa akatooma, ogimma, loosu rosichonna dandoo kaima assatenni ikkanna, koo-teemmate karso kaima assidhinota ikkitanno.
2. Boordete miilla batinyi uurrinshate deerri garinni ontunni kayse tonaa mittu geehshsha ikkara dandaanno.
3. Boordete miillanni mittu sayikkihu latishshu uurrinsha uurrinshu loosaasine mereerinni uurrinshu loosaasine xaphooma songonni dooramannoha ikkanno.
4. Ayee boordete miili lame mootimmate latishshu uurrinsha aleenni boordete miila ikke dooramara didandaanno.

ይሆናል፡፡

**9. ተጠያቂነት**

የልማት ድርጅቱ ዕዳ ሊሸፈን የሚችለው ድርጅቱ ባለው ሀብት ብቻ ይሆናል፡፡

**10.የልማት ድርጅቶች የአሰራር ሥርዓት**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ በመሆን የሚሠራ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግሥት የልማት ድርጅቶችን በቀጥታ ሊያሰራ ይችላል፡፡

**11.የልማት ድርጅት አደረጃጀት**

ማንኛዉም የልማት ድርጅት፡-

1. ቦርድ፤
2. ዋና ሥራ አስኪያጅ እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጅ፤ እና
3. ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**12.የልማት ድርጅቶች ቦርድ**

1. የቦርድ አባላት ምልመላ እና ምደባ ባላቸው ሥነ-ምግባር፣ ሙያ፣ ሥራ ልምድ እና ችሎታ ላይ የተመሠረተ ሆነው ፆታዊ ስብጥርን መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡
2. የቦርድ ዓባላት ብዛት እንደ ድርጅቱ ደረጃ ከአምስት እስከ አስራ አንድ ሊሆን ይችላል፡፡
3. ከቦርድ አባላት አንድ ሶስተኛዉ ከድርጅቱ ቋሚ ሠራተኞች መካከል በድርጅቱ ቋሚ ሠራተኞች ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ይሆናል፡፡
4. ማንኛዉም የቦርድ አባል ከሁለት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች በላይ የቦርድ አባል ሆኖ ሊመደብ አይችልም፡፡
5. ማንኛዉም የቦርድ አባል ተወዳደር የሆነ የሌላ ድርጅት ቦርድ አባል ሆኖ ሊመረጥ አይችልም፡፡

5. Ayee boordete miili hewisamaancho ikkitino wole uurrinsha miila ikke dooramara didandaanno.
6. Boordete miilla latishshu uurrinsha loosi aana sayissanno yannara loosu waagi baatooshshe baantanninsa.

**13. Boordete Miilla Loosu Yanna**

1. Boordete miili loosu yanna sase diro ikkitanna; layinkimeeshsho dooramiro mitte ledote loosu yanna owaatara dandaanno.
2. Konni Quwi cinaancho quwa (1) worroonnihu noo gedeenni hee'reenna boordete loosu rosichonna egennote reekko agarate yine ajay ajeenna mitto sayikki albaanni noori boordete miilla layinki doycho doorshi yannara haarunni riqiwama noonsa.

**14. Boordete Miiloomitte Uurritanno Ikkito**

1. Boordete miiloomitte aantete worroonni korkaatubbanni uurritara dandiitanno:
   a) Fajjosinni boordete miiloomittenni agurate xa'miriro;
   b) Bilchaantete anje korkaatinni looso garunni jeefisinokkiha ikkiro;
   c) Biilloonyisi ledo xaadinohunni woy wole ayee garinni ammana xeisate, awaawurate woy miilloommittete ikkado assitara dandiitannokki labbanno muishshu jaddubbanni hunaanchimmasi buuxanturo;
   d) Ikkadu korkaati nookkiha diru giddo sufamino sasenna hakkuy aleenni woy mittu baajeetete diri giddo ontenna hakkuy aleenni gambooshshunni gatinnoha ikkiro;
2. Konni Quwi cinaancho quwa (1) (a) garinni umisi fajjonni boordete miiloomittenni agura

6. የቦርዱ አባላት በድርጅቱ ሥራ ላይ ለሚያሳልፉት ጊዜ የሥራ ዋጋ ክፍያ ይከፈላቸዋል፡፡

**13.የቦርድ አባላት የስራ ዘመን**

1. የቦርዱ አባል የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ በድጋሚ ከተመረጠ ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ሊያገለግል ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቦርዱን የሥራ ልምድና የእውቀት ሽግግር ቀጣይነት ለመጠበቅ ሲባል ቢያንስ አንድ ሦስተኛ ነባር የቦርድ አባላት በሁለተኛ ዙር የአገልግሎት ዘመን ምርጫ ወቅት በአዲስ መተካት አለባቸው፡፡

**14.የቦርድ አባልነት የሚቋረጥበት ሁኔታ**

1. የቦርድ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-
   ሀ) በፍላጎቱ ከቦርድ አባልነት ለመልቀቅ ካመለከተ፤
   ለ) በብቃት ማነስ ምክንያት ሥራውን በአግባቡ ያልፈፀመ ከሆነ፤
   ሐ) ከኃላፍነቱ ጋር በተያያዘ ወይም በማናቸዉም ሌላ ሁኔታ በእመነት ማጉደል፣ በማጭበርበር ወይም ለቦርድ አባልነት ብቁ በማያደርግ ተመሳሳይ ወንጀል ጥፋተኝነቱ ከተረጋገጠ፤ ወይም
   መ) ያለ በቂ ምክንያት በዓመት ውስጥ በተከታታይ ሦስት እና ከዚያ በላይ ወይም በአንድ የበጀት ዓመት ውስጥ አምስት እና ከዚያ በላይ ጊዜ ከስብሰባ የቀረ ከሆነ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሠረት በገዛ ፍቃዱ ከቦርድ አባልነት መልቀቅ

hasi'rannohu boordete miili borrotenni boordete egensiisa noosi.

3. Boordete gambisaanchi konni Quwi cinaancho quwa (2) garinni shiqqinosi ku'laato iillitusi barri hanafe tonnu loosu barri giddo biilloonyeho egensiisa noosi.
4. Konni Quwi cinaancho quwi (1) (a) kayse (d) geeshsha xawinsoonni korkaatubbanni biilloonyu ayee boordete miila ayee yannara miiloomittete kaysara dandaanno. Miiloomittete kayinsoonni miili uurrinshu loosaaasine xaphooma songonni dooraminoha ikkiro biilloonyu xaphooma songora egensiisatenni wole doodhitanno gede assanno.

**15. Boordete Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Boordete hundaanchimma biilloonyeho ikkite aantete worroonni biilloonyinna loosu qeechi heerannose:

1. Latishshu uurrinsha loosose massagganno istiraatejenna ajuuja burqissanno;
2. Qara loosu ha'risaancho, layinki loosu ha'risaanchonna giddooydi odiite sooreessa hasiissanno akatoomu, ogimmate, loosu rosichinna dandoote safaraano garinni doorte ha'rinsho biilloonyeho egensiissanno, sumiimmete iillituro qaxartanno, gaantanno, loosunni geegiissitanno;
3. Qaru loosu ha'risaanchira hundaancho ikkitino loosu sooreeyye qixire, gaamooshshenna loosunni ka"a qaru loosu ha'risaanchiwiinni shiqquro buuxe kaajjishshanno;
4. Biilloonyu fushshanno damatte hanqafaancho

የሚፈልግ የቦርድ አባል በጽሁፍ ለቦርዱ ሰብሳቢ ማሳወቅ አለበት፡፡

3. የቦርድ ሰብሳቢውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) እስከ (መ) በተገለጹ ምክንያቶች መሠረት ባለሥልጣኑ ማንኛዉንም የቦርድ አባል በማንኛዉም ጊዜ ከአባልነት ማንሳት ይችላል፡፡ ከአባልነት የተነሳዉ የቦርድ አባል በድርጅቱ ቋሚ ሠራተኞች ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ አባል ከሆነ ባለሥልጣኑ ለጠቅላላ ጉባኤ ጉባኤ በማሳወቅ ሌላ እንዲመርጡ ያደርጋል፡፡

**15.የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር**

የቦርዱ ተጠሪነት ለባለስልጣኑ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የልማት ድርጅት ተግባሩን የሚመራበትን ስትራቴጂ እና ራዕይ ይቀርጻል፤
2. ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና የውስጥ ኦዲት ኃላፊ አስፈላጊ የሆኑ የሥነ ምግባር፤ የሙያ፤ የሥራ ልምድና የችሎታ መስፈርቶች መሠረት መርጠ ሂደቱን ለባለስልጣኑ ያሳዉቃል፣ መግባባት ላይ የተደረሰበትን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ከሥራ ያሰናብታል፤
3. ለዋና ሥራ አስኪያጁ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባና ከሥራ መነሳት በዋና ሥራ አስኪያጁ ሲቀርብለት መርምሮ ያጸድቃል፤
4. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መሠረታዊ ማዕቀፍ መሠረት ተጠንቶ የቀረበለትን የልማት

kaiminni xiinxallineenna shiqinoha latishshu uurrinshubba boordete miilla loosu waagi baatooshshe, loosu ha'risaanonna loosaasinete barru hoshsho baatooshshenna horo keenatenni woy umise xiinxallite biilloonyu ledo sumiimmete aana iillinoonnita kaajjishshanno, jeefishsha ha'runsitanno;

5. Biilloonyu woranno damatte hanqafo garinni latishshu uurrinshubba mannu wolqa gashshootinna loosu amuraate xiinxallatenni woy xiinxallisiisatenni loosu aana hossanno gede assitanno, jeefishshano ha'runsitanno;
6. Latishshu uurrinshubba giddooydi odiite qixirenna loosunni ka''a safaraanote garinni jeeefissanno, biilloonyeho egensiissanno;
7. Latishshu uurrinsha sokko ledo fiixoontanno istiratejike mixo yannate qixxeessatenni kaajjitanno gede biilloonyeho shiqishshanno, kaajjituro jeefissanno;
8. Latishshu uurrinsha dirunnita loosunna baajeetete mixo la''atenni biilloonyeho shiqishshanno, kaajjituro loosu aana hossanno gede assitanno, ha'runsitanno;
9. Latishshu uurrinsha mixo jeefishshi rippoorte yanna yannate keentanno, filiqishsha uytanno, biilloonyeho shiqqanno gede assitanno;
10. Biilloonyu diriirsanno keenote safaraanonna jawaachishshu amuraate kaima assatenni latishshu uurrinshubba sooreeyye keeno assitanno, jawaachishsha uytanno;
11. Latishshu uurrinsha xaphoomu polisenna giddooydi wodho kaajjishshanno;
12. Baajeetete diri goofihunni lewu agani giddo mootimmate tirfete qeecha latishshu fande

ድርጅቶች የቦርድ አባላት የሥራ ዋጋ፣ የሥራ አስኪያጆች እና የሠራተኞች አበል ክፍያና ጥቅም በመገምገም ወይም ራሱ አጥንቶ ከባለሥልጣኑ ጋር መግባባት ላይ የተደረሰበትን ያፀድቃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

5. ባለሥልጣኑ በሚያስቀምጠው መሠረታዊ ማዕቀፍ መሠረት የልማት ድርጅቱን የሰው ሀይል አስተዳደርና የአሰራር ሥርዓት በማጥናት ወይም በማስጠናት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
6. የልማት ድርጅቱን የውስጥ ኦዲተር ቅጥርና ከስራ መነሳት በመስፈርቱ ላይ በመመስረት ይፈፅማል፤ ለባለሥልጣኑ ያሳውቃል፤
7. የልማት ድርጅቱ ተልዕኮ ጋር የሚጣጣም ስትራቴጂካዊ ዕቅድ በወቅቱ ማዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤እንዲፀድቅ ለባለሥልጣኑ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ያስፈፅማል፤
8. የልማት ድርጅቱን የዓመታዊ የሥራና በጀት ዕቅድ በመመርመር ለባለስልጣኑ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤ ይከታተላል፤
9. የልማት ድርጅቱ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየጊዜው ይገመግማል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ ለባለሥልጣኑ እንዲቀርብ ያደርጋል፤
10. ባለሥልጣኑ በሚዘረጋው የመመዘኛ እና ማትጊያ ሥርዓት ላይ በመመሥረት የልማት ድርጅቱ ኃላፊዎችን ምዘና ያካሂዳል፤ ማትጊያ ይሰጣል፤
11. የልማት ድርጅቱን አጠቃላይ ፖሊሲ እና የዉስጥ ደንቦችን ይወስናል፤
12. የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በስድስት ወር ውስጥ የመንግሥት የትርፍ ድርሻን በልማት ፈንድ

akawuuntera eo ikkanno gede assitano;

13. Latishshu uurrinsha kaapitaale lexxitanno gede biilloonyeho hedo shiqishshanno;
14. Latishshu uurrinsha shallagote sanadda, shallagote xawishshanna faynaansete jeefishshi rippoorte yannate gobbaaydinna giddooydi odiiterootira hattono biilloonyeho shiqqanno gede assitanno;
15. Latishshu uurrinsha loosaasine loosinsa ledo amadamino qajeelshira gobbara hadhanno gara biilloonyeho egensiisatenni kaajjishshanno;
16. Biilloonyise hunda ubbannota uurrinshate hasiisaancho ikkitino uurrinshu jajjubba hiro mixote garinni kaajishshanno;
17. Latishshu uurrinsha shallagonna jajji garunni amadamasi qorqorsha assitanno;
18. Gamba assa dandiinannikki latishshu uurrinsha shallagubba buuxo assite biilloonyeho shiqishshanno; fajjinanni woyte jeefishsha ha’runsitanno;
19. Latishshu uurrinsha loossa massagate ogimmate ha’runsonna irko assitanno komite hasiishshisi garinni uurrissanno;

**16. Boordete Gambooshshu Yannanna Gumulo Sayissanno Amuraate**

1. Boorde sasu aganinni mitte higge uurrinshu gambooshshe assitanno.
2. Uurrinshu gambooshshi ajandi balaxe boordete miillara iillanno assinanni.
3. Wiinama ikkito xaadduro woy boordete miilla mereerinni bocu aleenni ikkitannori xa’mituro boordete gambisaanchi wiinamu gambooshshe woshshanno.

ሂሳብ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፤

13. የልማት ድርጅቱ ካፒታል እንዲጨምር ለባለሥልጣኑ ሀሳብ ያቀርባል፤
14. የልማት ድርጅቱን የሂሳብ ሰነዶችን፣የሂሳብ መግለጫና የፋይናንስ አፈፃፀም ሪፖርት በወቅቱ ለውጭ እና ውስጥ ኦዲተሮች እንዲሁም ለባለሥልጣኑ እንዲቀርብ ያደርጋል፤
15. የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች ከስራቸው ጋር በተያያዘ ወደ ውጭ ሀገር ለሥልጠና ስለሚሄዱበት ሁኔታ ለባለስልጣኑ በማሳወቅ ያፀድቃል፤
16. በሥልጣኑ ሥር ያለዉን ለድርጅቱ ወሳኝ የሆኑ የቋሚ ንብረት ግዥዎች በዕቅድ ላይ በመመሥረት ያፀድቃል፤
17. የልማት ድርጅቱ ሂሳብ እና ንብረቶች በአግባቡ መያዛቸውን ይቆጣጠራል፤
18. ሊሰበሰቡ የማይችሉ የልማት ድርጅቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን መርምሮ ለባለሰልጣኑ ያቀርባል፤ ሲወሰንም አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
19. የልማት ድርጅት ተግባራትን ለመምራት የሙያ ክትትል እና ድጋፍ ኮሚቴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል፡፡

**16. ስለቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የዉሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት**

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. የመደበኛ ስብሰባ አጀንዳ ቅድሚያ ለቦርዱ አባላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
3. አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ ከጠየቁ የቦርዱ ሰብሳቢ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
4. ከቦርድ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ

4. Boordete miilla mereero bocu aleenni ikkitannori leelturo gambooshshu guutaho.
5. Boordete gumulo roore huuronni sa’annoha ikkanna, huuro taaloho beehanturo boordete gambisaanchinni irkisantanno hedo boordete gumulo ikkitanno.
6. Boordete borreessaanchi uurrinshate loosaasine mereerinni loosu ha’risaanchinni doorame huuriweelo beeqqanno; gambooshshu songaale amadanno.
7. Uurrinshate loosu ha’risaanchi boordete gambooshshira xawishsha aannoha ikke huuroweelo beeqqanno.
8. Konni Quwi cinaancho quwi (1) kayse (8) worroonnihu agaramino gede heereenna, boorde umise gambooshshu amuraate fushshitara dandiitanno.

**17. Boordete Miilla Xa’mamooshshe**

1. Ayee boordete miili:
   a) Yawosi qorophotenninna bilchaantete fulate;
   b) Loosu korkaatinni afi’rino latishshu uurrinsha maafuda taje uurrinshate hajo gobbaanni ho’roonsira hoogate;
   c) Rosamino loosisi woy biilloonyisi latishshu uurrinsha horo ledo kiphi yitannota ikkituro boordete egensiisatenni umisi hasattonni miiloomitte agurate yawo noosi.
2. Konni Lallawi kaiminni looso garunni jeefisa hoogate kainnohunni uurrinshate aana iillanno ayee gawajjo addinninna gutunni xa’mamooshshu hee’ranno.
3. Boordete miilla gutunni gumultanno gumulora gutu yawo heedhanonsa.

የሚሆኑት ከተገኙ ስብሰባው ይካሄዳል፡፡

5. የቦርዱ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ የሚተላለፍ ሆኖ፤ ድምፅ እኩል ከተከፈለ በቦርዱ ሰብሳቢ የተደገፈው ሀሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡
6. የቦርዱ ጸሐፊ ከድርጅቱ ሠራተኞች መካከል በሥራ አስኪያጁ ተወክሎ ያለ ድምፅ ይሳተፋል፤ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡
7. የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በቦርድ ስብሰባ ላይ አስረጂ ሆኖ ያለ ድምፅ ይሳተፋል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(1) እስከ (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**17. የቦርድ አባላት ተጠያቂነት**

1. ማንኛውም የቦርድ አባል፡-
   ሀ) ኃላፍነቱን በጥንቃቄ፤ በብልሀትና በትጋት የመወጣት፤
   ለ) በሥራው ምክንያት ያገኘውን የልማት ድርጅቱን ሚስጥራዊ መረጃ ከድርጅቱ ጉዳይ ውጪ ያለመጠቀም፤
   ሐ) መደበኛ ሥራው ወይም ሃላፊነቱ ከልማት ድርጅቱ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ከሆነ ለቦርዱ በማሳወቅ በፍላጎቱ ከአባልነት የመልቀቅ ኃላፍነት አለበት፡፡
2. በዚህ አዋጅ መሠረት ተግባሩን በአግባቡ ባለመፈጸሙ የተነሳ በድርጅቱ ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጉዳት የተናጥልና የጋራ ተጠያቂነት ይኖረዋል፡፡
3. የቦርድ አባላት በጋራ ለሚወስኑት ውሳኔ የጋራ ሀላፊነት ይኖራቸዋል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ

4. Konni Quwi cinaanchu quwi (3) worronniri noo gedeenni heereenna gumulo uyni yannara gumulo giwino miili hedosi songaalete safareenna malaatise xa’mamatenni gatanno.

**18. Qaru Loosu Ha’risaanchi Hundaanchimma, Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Latishshu uurrrinsha qaru loosu ha’risaanchi hundaanchimma boordete ikkiteenna aantete worroonni biilloonyinna loosu qeechi hee’rannosi:

1. Latishshu uurrinshara uynoonni biilloonyenna loosu qeecha loosu aana hosiisanno;
2. Latishshu uurrinshaha barru barrunku looso aliidimmatenni massaganno, gashshanno, harunsanno;
3. Latishshu uurrinsha looso mixi’ranno, tantananno, massaganno, gashshanno, qorqoranno;
4. Latishshu uurrinsha istratejike mixo qixxeesse boordete shiqishanno, kaajjituro jeefisanno, jeefisiisanno;
5. Latishshu uurrinsha loosunna baajeetete mixo qixxeesse boordete shiqishanno, kaajjituro loosu aana hosiisanno;
6. Latishshu uurrinsha mixote jeefishshi rippoorte boordete shiqishanno, uynanni filiqqishshi garinni loosu aana hosiisanno;
7. Latishshu uurrinsha sayikki bisi ledo assitanno loosu xaadooshshira uurrrinsha lekkisanno;
8. Hundaanchimmansa qaru loosu ha’risaanchira ikkitino loosu sooreeyyeha hasiissanno akatoomu, ogimmate, loosu rosichinna dandoote safaraano garinni doore

ውሳኔውን የተቃወመ አባል ሀሳቡን ቃለ ጉባኤ ላይ በማስፈርና በመፈረም ከተጠያቂነት ነፃ ይሆናል፡፡

**18. የዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠርነት፣ ሥልጣንና ተግባር**

የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነት ለቦርድ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለልማት ድርጅቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያዉላል፡፡
2. የልማት ድርጅቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች በበላይነት ይመራል፤ ያስተዳድራል፤ይቆጣጠራል፡፡
3. የልማት ድርጅቱን ሥራ ያቅዳል፣ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያሥተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤
4. የልማት ድርጅቱን ስትራቴጅክ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ይፈፅማል፣ ያስፈጽማል፤
5. የልማት ድርጅቱን የሥራ እና የበጀት ዕቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፤
6. የልማት ድርጅቱን የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ለቦርዱ ያቀርባል፣ በሚሰጠው ግብረ-መልስ መሠረት ሥራ ላይ ያውላል፤
7. ልማት ድርጅቱ ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው የሥራ ግንኙነት ድርጅቱን ይወክላል፤
8. ተጠሪነታቸው ለዋና ሥራ አስኪያጅ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎች አስፈላጊ የሆኑ የሥነ ምግባር፤ የሙያ፤ የሥራ ልምድና የችሎታ መስፈርቶች መሠረት መርጦ ሂደቱን ለቦርዱ ያሳዉቃል፣ መግባባት ላይ የተደረሰበትን ይቀጥራል፣

ha’rinsho boordete egensiisanno, sumiimmete iillituro qaxaranno, gaamanno, loosunni geegiissanno;

9. Loosiisannohunna loosaasinete seerubba garinni latishshu uurrinsha loosaasine qaxaranno, gashshanno, loosunni geeggiissano;
10. Latishshu uurrinsha jajja gashshanno;
11. Biilloonyu assanno loosu keenora rippoorte shiqishanno, xawishsha aanno;
12. Latishshu uurrinsha shallago yannate loosiisatenni woy gobbaaydi odiiterenni qorqorsiisatenni rippoorte shiqishanno;
13. Afantino buuxantino tirfenni seeruy murroonniha mootimmate tirfete qeecha yannatenni latishshu fandera eo ikkanno gede assanno;
14. Latishshu uurrinsha loosaasine mittimmate sumiimmeta safote sanade boordete shiqishanno, boorde uytanno tashshote hedo lede sumuumme malaatisanno;
15. Boordete muro jeefisanno, jeefisiisanno;
16. Woloota boordenni uynanni ledote loossa loosanno.

**19. Layinki Loosu Ha’rinsaanchi Biillonyenna Loosu Qeecha**

1. Qaru loosu ha’risaanchinni uynannisi loosu biddissi kaiminni latishshu uurrinsha looso mixi’ratenni, tantanatenni, massagatenninna qineessatenni qara loosu ha’risaancho kaa’lanno.
2. Qaru loosu ha’risaanchinni uynannisi wolootta loossa loosanno.
3. Qaru loosu ha’risaanchi hee’rannokki yannara lekkise loosanno.

**20. Qarunna Layinki Loosu Ha’risaanchi Xa’mamooshshe**

Wolootta seerubbara worroonniri noo gedeenni heereenna, ayee latishshu uurrinsha qaru loosu ha’risaanchi woy layinki loosu ha’risaanchi loososi jeefisanno yannara de’netenni woy afanni heere uurrinshate aana iillishanno gawajjora

ይመድባል፣ ከሥራ ያሰናብታል፤

9. በአሰሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት የልማት ድርጅቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤ ከሥራ ያሰናብታል፤
10. የልማት ድርጅቱን ንብረት ያስተዳድራል፤
11. ባለሥልጣኑ በሚያካሂደው የሥራ ግምገማ ላይ ሪፖርት ያቀርባል፤ ማብራሪያ ይሰጣል፤
12. የልማት ድርጅቱን ሂሳብ በወቅቱ በማሰራት ወይም በውጪ ኦዲተር በማስመርመር ሪፖርት ያቀርባል፤
13. ከተገኘው የተጣራ ትርፍ በሕግ የተወሰነውን የመንግሥት የትርፍ ድርሻ በወቅቱ ወደ ልማት ፈንድ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፤
14. የልማት ድርጅቱ ሠራተኞች የህብረት ስምምነት ረቂቅ ለቦርድ ያቀርባል፤ቦርዱ የሚሰጠውን የማስተካከያ ሀሳብ በማካተት ስምምነቱን ይፈርማል፤
15. የቦርዱን ውሳኔዎች ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል፤
16. ሌሎች በቦርድ የሚሰጡ ተጨማሪ ተግባራት ያከናዉናል፡፡

**19. የምክትል ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር**

1. ከዋና ሥራ አስኪያጁ በሚሰጠው የስራ መመሪያ መሠረት የልማት ድርጅቱን ተግባራት በማቀድ፤ በማደራጀት፤ በመምራትና በማስተባበር ዋና ሥራ አስኪያጁን ያግዛል፤
2. በዋና ሥራ አስኪያጅ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤
3. ዋና ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፡፡

**20. የዋና እና የምክትል ሥራ አስኪያጅ ተጠያቂነት**

በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ

garimma noosi seeri garinni xa’mamannoha ikkanno.

## GAFA SASE

## LATISHSHU UURRINSHUBBA KAAPITAALE

**21. Kaapitaalete Buicho**

Latishshu uurrinshubba uurrisate kaapitaale mootimmatenni gaammanni baajeete woy wole buichonni ikkitanno.

**22. Baantoonni Kaapitaale**

Ayee latishshu uurrinsha uurritanno yannara fajjinoonni kaapitaale giddonni baantoonni kaapitaale bikki lemiina onte xibbunni anganna hakkuyi aleenni ikka noosi.

**23. Fajjinoonni Kaapitaale**

1. Fajjinoonni latishshu uurrinshubba kaapitaale uurrinsha uurritu barrinni hanafe ontu diri giddo wo’munni wo’ma baatante goofa noose.
2. Konni Quwi cinaancho quwa (1) garinni latishshu uurrinshubbara fajjinoonni kaapitaale murroonni yanna giddo baatante gooffinokkiha ikkiro biilloonyu sayikki bisi qoosso kisikkinni uurrinshate kaapitaale baantoonni kaapitaale bikkiwa ajjanno gede muro saysara dandaanno.

**24. Kaapitaale Leda**

Latishshu uurrinshara ledote kaapitaale hasiissannoseta ikkase uurrinshate boordenni xa’mo shiqquro biilloonyu shiqqinnota xa’mo buuxatenni mootimmate murote hedo shiqishe lexxitanno gede assara dandaanno.

**25. Kaapitaale Ajisha**

Latishshu uurrinsha kaapitaale aantete worroonni ikkitubbanni sayikki bisi horo kissukkinni ajisha

ማንኛውም የልማት ድርጅቶች ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ በቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ በድርጅቱ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የልማት ድርጅቶች ካፒታል

**21. የካፒታል ምንጭ**

የልማት ድርጅቶች የመቋቋሚያ ካፒታል በመንግሥት የሚመደብ በጀት ወይም ከሌላ ምንጭ ይሆናል፡፡

**22. የተከፈለ ካፒታል**

ማንኛውም የልማት ድርጅት በሚቋቋሚበት ጊዜ ከተፈቀደው ካፒታል ውስጥ የተከፈለው ካፒታል መጠን ሃያ አምስት ፐርሰንት እና ከዚያ በላይ መሆን አለበት፡፡

**23. የተፈቀደ ካፒታል**

1. የተፈቀደው የልማት ድርጅቶች ካፒታል ድርጅቱ ከተቋቋመበት ቀን ጀምሮ በአምስት ዓመት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ መጠናቀቅ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለልማት ድርጅቶች የተፈቀደ ካፒታል በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ ከሆነ ባለሥልጣኑ የሦስተኛ ወገን መብትን ሳይነካ የድርጅቱን ካፒታል ወደ የተከፈለው የካፒታል መጠን እንዲያንስ ሊወስን ይችላል፡፡

**24. ካፒታል ስለመጨመር**

ለልማት ድርጅት ተጨማሪ ካፒታል የሚያስፈልግ መሆኑ በድርጅቱ ቦርድ ጥያቄ ሲቀርብ ባለሥልጣኑ የቀረበውን ጥያቄ በመመርመር ለመንግሥት የውሳኔ ሃሳብ በማቅረብ እንድጨምር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**25. ካፒታል ስለመቀነስ**

የልማት ድርጅት ካፒታል በሚከተሉት ሁኔታዎች የሶስተኛ ወገንን ጥቅም ሳይነካ ሊቀንስ ይችላል፡-

dandiinanni:

1. Latishshu uurrinsha kaapitaale ajjanno gede gobbaaydi odiiterenni hedo shiqquro;
2. Latishshu uurrinshara fajjinoonni kaapitaale wo'munni wo'ma baatante gooffinokkiha ikkiro.

## GAFA SHOOLE

## LATISHSHU UURRINSHUBBA DADDALU SU'MANNA MALAATE

### 26. Latishshu Uurrinsha Su'ma

1. Ayee latishshu uurrinsha su'mi:
   a) Loososi loosanno su'ma ikke, uurrinshate looso faajjete xawisannoha;
   b) Seeranna dagate mooraale ledo kiphamannokkiha hattono sayikki bisi qoosso kisannokkiha;
   c) Uurrinshate loosu basera xawoho leella noosi.
2. Ayee latishshu uurrinsha su'ma doorate gari garimma noosi bisinni buuxama noosi;
3. Ayee latishshu uurrinsha konni Lallawinna wolootta garimma noonsa seerubba sa''atenni su'misinni horoonsidhinoha ikkiro garimma noosi seerinni xa'mantannoha ikkanno.

### 27. Latishshu Uurrinsha Daddalu Malaate

1. Ayee latishshu uurrrinsha laashshitanno laalcho woy uytanno owaante xawissannonna woloотu uurrrinshubbawiinni baxxitanno daddalu malaati heerasera hasiissanno.
2. Ayee latishshu uurrinsha daddalu malaate doodhitanno yannara seerunna dagate mooraale ledo kiphamannokkihanna sayikki bisi qoosso

1. የልማት ድርጅቱ ካፒታል እንዲቀንስ በውጪ ኦዲተር ሃሳብ ሲቀርብ፤
2. ለልማት ድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ ያልተጠናቀቀ ሲሆን፡፡

## ክፍል አራት

## የልማት ድርጅቶች የንግድ ስም እና ምልክት

### 26. የልማት ድርጅት ስም

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት ስም፡-
   ሀ) ሥራውን የሚያከናውንበት ስም ሆኖ የድርጅቱን ተግባር በግልፅ የሚያመለክት፤
   ለ) ከሕግና ህብረተሰቡ ሞራል ጋር የማይቃረን እና የሶስተኛ ወገንን መብት የማይነካ፤
   ሐ) በድርጅቱ የሥራ ቦታ በግልፅ መታየት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም የልማት ድርጅት ስም አመራረጥ አግባብ ባለው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውም የልማት ድርጅት የዚህን አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጎች በመተላለፍ በስሙ የተጠቀመ እንደሆነ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሠረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

### 27.የልማት ድርጅት የንግድ ምልክት

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት የሚያመርተውን ምርት ወይም የሚሰጠውን አገልግሎት የሚገልፅና ከሌሎች ድርጅቶች የሚለይበት የንግድ ምልክት ሊኖረው ይገባል፡፡

kisannokkiha ikkasi garimma noosi bisi buuxa hasiissanno;

3. Ayee daddalu malaati loosu aana hosasira albaanni garimma noosi bisinni borreessame hala'ladunni fincamanno gaazeexi aana attamame fulanno assinanni.

## GAFA ONTE

## LATISHSHU UURRINSHUBBA HIRO, JAJJU GASHSHOOTINNA SHALLAGOTE AMADOOSHSHI AMURAATE

**28. Hirotenna Jajju Gashshoote**

Ayee latishshu uurrinsha hirotenna jajju gashshooti amuraati xanbe, fulo ajishatenna hegere horaameessima kaima assirinoha ikka noosi. Tittirsha biiloonyu fushshanno biddissinni murranni.

**29. Shallagote Amadooshshi Amuraate**

Ayee latishshu uurrinsha xaphoomu daddalu amuraati garinni adhamooshshu nooha shallagote amadooshshe harunsinoha ikkanno.

**30. Baajeetete Diri, Shallago Cufatenna Faynaansete Rippoorte**

1. Ayee latishshu uurrinsha baajeetete diri Maaja 1 kayse Ella 30 geeshsha ikkanno.
2. Ayee latishshu uurrinsha dirunni mitte higge shallago cufa noose.
3. Diru shallago baajeetete diri goofihunni lamu agani giddo cufante gobbaaydi odiitera fano ikka noose.
4. Ayee latishshu uurrinsha diru shallago loosu jeefishshi gara baajeetete diri goofihunni lamu agani giddo rippoorte qixxeesatenni

2. ማንኛውም የልማት ድርጅት የንግድ ምልክት በሚመርጥበት ጊዜ ከሕግና ህብረተሰቡ ሞራል ጋር የማይቃረንና የሶስተኛ ወገን መብት የማይነካ መሆኑን አግባብነት ባለው አካል ማረጋገጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም የንግድ ምልክት ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት አግባብነት ባለው የመንግሥት አካል ተመዝግቦ በሰፊዉ በሚሰራጭ ጋዜጣ ላይ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## የልማት ድርጅቶች ግዥ፣ንብረት አስተዳደር እና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት

**28. ግዥና ንብረት አስተዳደር**

ማንኛዉም የልማት ድርጅት ግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት ግልፅነትን፣ ወጪ ቆጣቢነትን እና ዘላቂ ጠቀሜታን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ዝርዝሩ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**29. የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት**

ማንኛውም የልማት ድርጅት በጠቅላላ ንግድ አሠራር ተቀባይነት ያለዉ የሂሳብ አያያዝ የተከተለ ይሆናል፡፡

**30. የበጀት ዓመት፣ ሂሳብ መዝጋት እና የፋይናንስ ሪፖርት**

1. የማንኛውም የልማት ድርጅት የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የልማት ድርጅት በዓመት አንድ ጊዜ ሂሳቡን መዝጋት ይኖርበታል፡፡
3. ዓመታዊ ሂሳቡ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ተዘግቶ ለውጪ ኦዲተር

biilloonyeho shiqisha noose.

**31. Seeraawe Rizerve Shallagonna Horoonsishsha**

1. Ayee latishshu uurrinshara seeraawe reserve shallago heedhanose.
2. Ayee latishshu uurrinsha afidhino buuxamino tirfinni onte xibbunni diru dirunkunni uurrinshate kaapitaale 20 xibbunni iilllita geeshsha seeraawe rizervera wora noose.
3. Seeraawe rezerve iillanno kisaara baatate, hendoonnikki fulo woy asale baatate hossara dandiitanno.

**32. Gabbaronna Taakisete Baatooshshe**

Latishshu uurrinshubba woloottu seerubbanni uynoonni gabbarotenna taakisete baatooshshinni gatate qoosso agarante heedheenanni, mootimmate gabbaronna taakise baattanno.

**33. Gobbaaydi Odiitere Gaama**

1. Sidaamu qoqqowi Qara Odiite Loosu Mini seerunni uyinoonni biilloonyinna loosi agarame hee'reennanni, ayeetano latishshu uurrinsha shallago gobba odiiterenni buuxanno.
2. Gobbaaydi odiitere keeshshote yanna biilloonyu murannota ikkite sufishshu noosi sase baajeetete diro roora dinose.
3. Gaamamannohu gobbaaydi odiitere ogimma, akatoommenna dandoo lainohunni Qoqqowu Qara Odiitete Loosu Mini fushshanno safaraano wonshannoha ikka noosi.

**34. Shallago Qorqorsiisate Gadacho**

Qorqorranniti latishshu uurrinsha woxe woy uurrinshu jajja adhinohu woy fulo assinohu, baatinohu woy shallagote sooreessa ikkinohu

ክፍት መሆን አለበት፡፡

4. ማንኛውም የልማት ድርጅት የዓመት ሂሳብ ሥራ አፈጻጸም ሁኔታ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ሪፖርት በማዘጋጀት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

**31. የህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና አጠቃቀም**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት ሕጋዊ የሆነ የመጠባበቂያ ሂሳብ ይኖረዋል፡፡
2. ማንኛውም የልማት ድርጅት ካገኘው የተጣራ ትርፍ አምስት በመቶውን በየአመቱ የድርጅቱ ካፒታል 20 በመቶ እስከሚደርስ ድረስ ወደ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሳቡ ፈሰስ ማድረግ አለበት፡፡
3. የሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ የሚደርሰውን ኪሣራ ለመሸፈን፣ ላልታሰበ ወጪ ወይም የዕዳ ክፍያን ለመሸፈን ሊውል ይችላል፡፡

**32. የግብርና ታክስ ክፍያ**

የልማት ድርጅቶች በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ከግብር እና ታክስ ነፃ የመሆን መብታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግሥት ግብር እና ታክስ ይከፍላሉ፡፡

**33. የዉጭ ኦዲተር አመዳደብ**

1. ለሲዳማ ክልል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በሕግ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የማንኛውም የልማት ድርጅት ሂሳብ በውጭ ኦዲተር ይመረመራል፡፡
2. የውጪ ኦዲተሮች የቆይታ ጊዜ በባለሥልጣኑ የሚወሰን ሆኖ ከተከታታይ ሦስት የበጀት ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡
3. የሚመደበው የውጪ ኦዲተር ሙያ፣ ሥነ ምግባር እና ችሎታ በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሚወጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

**34. ሂሳብ የማስመርመር ግዴታ**

የተመርማሪውን የልማት ድርጅት ገንዘብ ወይም ቋሚ ንብረት የተረከበ ወይም ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም የሂሳብ ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው በውጭ ኦዲተር ወይም በውስጥ ኦዲተር በሚጠየቅበት ጊዜ ሂሳቡን የማስመርመርና አስፈላጊውን መረጃ

ayee manchi gobbaaydi odiiterenni woy giddooydi odiiterenni xa'minanni yannara shallago qorqorsiisatenna hasiissanno taje shiqishate gadacho noosi.

**GAFA LEE**

**LATISHSHU UURRINSHUBBA KARSAMA, BEEHAMA WOY DIIGAMA**

**35. Tuuqqa Wodhi-woro**

1. Latishshu uurrinshubba karsama woy beehama xiinxallote aana xintantinota ikka noose.
2. Latishshu uurrinshubba karsama woy beehama mootimmatenna dagate horo hattono sayikki bisi qoosso gawajjitannokki garinni gumulama noose.

**36. Latishshu Uurrinshubba Karsama, Beehama woy Hirama**

1. Qoqqowu jeefisiisaanote amaale mini latishshu uurrinshubba karsantanno, beehantanno woy hirantanno gede gumulara dandaanno. Tittirsha fultanno wodhonni gumallanniha ikkanno.
2. Latishshu uurrinshubba karsamanna diigama lainohunni haaru Daddalu Seeri Quwa 565 kayse quwa 577 geeshsha worroonniri hasiishshisi garinni jeefisamannoha ikkanno.

**37. Qoossonna Gadacho Saysa**

1. Karsantino latishshu uurrinshubba qoossonna gadacho haaro uurritanno latishshu uurrinshara sa'anno.
2. Beehamatenni haaro latishshu uurrinshubba ikkite tantanantino latishshu uurrinshubba mereero noo qoossonna gadacho beehantanno gara biilloonyunni qixxaabbe qoqqowu

የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

**ክፍል ስድስት**

**የልማት ድርጅቶች መዋሐድ፣ መከፈል ወይም መፍረስ**

**35. መሠረታዊ መርህ**

1. የልማት ድርጅቶች መዋሀድ ወይም መከፈል ጥናት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፤
2. የልማት ድርጅቶች መዋሀድ ወይም መከፈል የመንግሥትና ህዝብን ጥቅም እንዲሁም የሶስተኛ ወገን መብት በማይጎዳ ሁኔታ መፈጸም አለበት፡፡

**36. የልማት ድርጅቶች መዋሀድ፣ መከፈል ወይም መሸጥ**

1. የክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት የልማት ድርጅቶች እንዲዋሂዱ፣ እንዲከፈሉ ወይም እንዲሸጡ ሊወስን ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. የልማት ድርጅቶች መዋሂድ እና መፍረስ በተመለከተ የአዲሱ ንግድ ሕግ አንቀጽ 565 እስከ አንቀጽ 577 እንደአግባብነታቸዉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**37. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ**

1. የተዋሃዱት የልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታ አዲስ ወደ ተመሠረተው ድርጅት ይተላለፋል፡፡
2. በመከፈል አዲስ የልማት ድርጅቶች በመሆን የተደራጁ የልማት ድርጅቶች መካከል ያለው

jefisiisaanote bissa amaale minira shiqqe gumulantanno.

3. Beehantanno latishshu uurrinshubba beehamansara albaanni sayikki bisira e'ino gadacho heedhuro haaro xintantanno uurrinshubba hojjinna gutu xa'mamooshshi heeranonsa.

**38. Diigamate Korkaatubba**

Ayee latishshu uurrinshubba aantete worroonni korkaaatubbanni diigantara dandiitanno:

1. Latishshu uurrinsha seeri giddo worroonni keeshshote yanna gooffuro;
2. Latishshu uurrinsha uurritinno loosi goofiro;
3. Latishshu uurrinsha xintantino hexxo jeefisa hoogguro woy ayee garinni jeefisa dandiitannokkiha ikkiro;
4. Latishshu uurrinshara baantoonni kaapitaale giddo ontawo xibbunninna hakkuy aleenni ba'uro woy kassarturo;
5. Qoqqowu jefisiisaanote amaale mini latishshu uurrinsha diigantara gumuliro;
6. Latishshu uurrinsha kassartinota yoote mini gumuliro.

**39. Shallago Qorqorate Ha'rinshonna Diigamate Gumulo**

1. Latishshu uurrinsha diigantannoha ikkiro shallago buuxama noose.
2. Ayee latishshu uurrinsha diigantanno gede gumulliro shallago buuxo assitannori gaamantannonna qoosso noonsari shallago buuxate ha'rinsho affanno gede assinanni.
3. Diigantino latishshu uurrinsha ledo amadisiisantannoti ayee manchi qoosso konni Lallawinninna garimma noonsa seerubba

መብትና ግዴታ የሚከፋፈልበት ሁኔታ በባለስልጣኑ ተዘጋጅቶ ለክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት ቀርቦ ይወሰናል፡፡

3. የተከፈሉ የልማት ድርጅቶች ከመከፈላቸው በፊት ለሶስተኛ ወገን የገቡት ግዴታ ካለ አዲስ የተመሠረቱ ድርጅቶች የተናጠልና የጋራ ተጠያቂነት ይኖራቸዋል፡፡

**38. የመፍረስ ምክንያቶች**

ማንኛውም የልማት ድርጅት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፡-

1. በልማት ድርጅቱ ማቋቋሚያ ሕግ ውስጥ የተደነገገው የቆይታ ጊዜ ሲያበቃ፤
2. የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበት ስራ ሲያልቅ፤
3. የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበትን አላማ ሳያሳካ ሲቀር ወይም በምንም አይነት ሊፈጸም የማይችል ሲሆን፤
4. ለልማት ድርጅቱ ከተከፈለዉ ካፒታል ዉስጥ ሀምሳ በመቶ እና ከዚያ በላይ ሲጠፋ ወይም ሲከስር፣
5. የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት የልማት ድርጅቱ እንዲፈርስ ሲወስን፣
6. የልማት ድርጅቱ መክሰሩን ፍርድ ቤት ሲወስን፡፡

**39. ሂሳብ የማጣራት ሂደትና ስለመፍረስ ውሳኔ**

1. የልማት ድርጅት የሚፈርስ ከሆነ ሂሳቡ መጣራት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የልማት ድርጅት እንዲፈርስ ሲወሰን የሂሳብ አጣሪዎች እንድመደቡ እና ባለመብቶቹ ሂሳብ የማጣራት ሂደትን እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡
3. ከፈረሰው የልማት ድርጅት ጋር የሚያያዝ የማንኛውም ወገን መብት በዚህ አዋጅና

xintinni agarantannoha ikkanno.

4. Biilloonyu hajo la’anno bisinni kaajjinoha diiigantanno uurrinshaha jirotenna asalu xawishsha goofimarchu ripoorte gumulote hedo ledo qoqqowu jefisiisaanote bissa amaale minira shiqishatenni uurrinsha uurritino seeri shaaramanno gede assanno.
5. Diigantino latishshu uurrinsha sanaddanna mazigabba tonnu dirira amanyootunni biilloonyunni amadama hasiissanno.
6. Diigantino latishshu uurrinsha mazigabba qorqorara hasi’ranno bisi owaantete baatooshshe jeefisatenni qorqora dandaanno.
7. Latishshu uurrinshubba diigama lainohunni uynanni gumulo hala’le fincamanno gaazeexira attamante fula noose.

## GAFA LAMALA

## LATISHSHU FANDE UURRISANNIRE

**40. Latishshu Fande Uurrisanna Gashshannire**

Jeefisiisaanote Amaale Mini latishshu fande uurritannonna galtanno gara wodhotenni gumulanno.

## GAFA SETTE

## ADDI ADDI WORO

**41. Gadacho**

1. Ayee latishshu uurrinsha biilloonyunni uynoonni seeraawe biddissa adhatenni loosu aana hosiisate gadacho noosi.
2. Konni Quwi cinaancho quwa (1) garinni uynanni biddissi borrotenni ikka noosi.

አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡

4. ባለሥልጣኑ ጉዳዩ በሚመለከተው አካል የፀደቀውን የሚፈርሰውን ድርጅት የሀብትና ዕዳ ማብራሪያ የመጨረሻ ሪፖርት ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለክልሉ የአስፈጻሚ አካለት ምክር ቤት በማቅረብ ድርጅቱ የተቋቋመበት ሕግ እንዲሻር ያደርጋል፡፡
5. የፈረሰ የልማት ድርጅት ሰነዶችና መዝገቦች ለአስር ዓመት በሥርዓት በባለስልጣኑ ሊያዝ ይገባል፡፡
6. የፈረሰ የልማት ድርጅት መዝገቦች መመርመር የሚፈልግ አካል የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም ሊመረምር ይችላል፡፡
7. የልማት ድርጅቶች መፍረስ በተመለከተ የሚሰጠው ውሳኔ በሰፍዉ በሚሰራጭ ጋዜጣ ታትሞ መውጣት አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## የልማት ፈንድ ስለመቋቋም

**40. የልማት ፈንድ ስለማቋቋምና ስለማስተዳደር**

የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት የልማት ፈንድ የሚቋቋምበትና የሚተዳደርበትን ሁኔታ በደንብ ይወስናል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**41. ግዴታዎች**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት ከባለሥልጣኑ የሚሰጠውን ሕጋዊ መመሪያ በመውሰድ ሥራ ላይ የማዋል ግዴታ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት

3. Wolootu seerubbara worroonnihu noowa heereenna, latishshu uurrinsha massagaano uynoonni seeru biddissa adhatenni loosu aana hosiissannokkiha ikkiro biilloonyu taashshate qaafo adhanno, la'annosi bisira egensiisanno.

**42. Rippoortenna Keenote Amuraate**

Loosu jeefishshi ripportenna keenote amuraate biilloonyu fushshanno biddissinni murranniha ikkanno.

**43. Dagoomitte Owaante Aate Gadacho**

1. Ayee latishshu uurrinsha noose sokkonna mixo ledo xaadooshshe afidhino dagoommitte owaante qooxeessu dagara aa noose.
2. Uytanno owaante uduunnichunninna womaashshunni ikkite uurrinshate diru mixo giddo hanqafante kaajja noose.
3. Uytannoti dagoomitte owaante dagoomittenna miinju hattono kalaqamu jiro agarooshshi iima illachishshinota ikkite garimma noonsa seerubbara worroonni qansichimmate owaante hanqaffanno.

**44. Reekkote Woro**

Balaxxe tantanate wodhonni uurritinnori latishshu uurrinshubba konni Lallawinni uurritinno gede assine adhinanniha ikkeenna qoossonsanna gadachonsa suffannoha ikkanno.

**45. Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye**

1. Lallawa jeefisate hasiissanno Wodho qooqqowu jeefisiisaanote amaale mini fushshara dandaanno.
2. Biillonyu Lallawano ikko Wodho jeefisate hasiissanno Biddissubba fushshara dandaanno.

የሚሰጠው መመሪያ በፅሁፍ መሆን አለበት፡፡

3. በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የልማት ድርጅቱ አመራር የተሰጠውን ሕጋዊ መመሪያ በመውሰድ ሥራ ላይ የማያውል ከሆነ ባለስልጣኑ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

**42.የሪፖርትና ግምገማ ሥርዓት**

የሥራ አፈፃፀም ሪፖርትና ግምገማ ሥርዓት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

**43.ማህበራዊ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ**

1. ማንኛውም የልማት ድርጅት ካለው ተልዕኮ እና አላማ ጋር ግንኙነት ያለው ማህበራዊ አገልግሎት ለአከባቢው ህብረተሰብ መስጠት አለበት፡፡
2. የሚሰጠው አገልግሎት በዓይነትና በገንዘብ ሆኖ በድርጅቱ ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ ተካትቶ መጽደቅ አለበት፡፡
3. የሚሰጠው የማህበራዊ አገልግሎት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ላይ የሚያተኩር ሆኖ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ የዜግነት አገልግሎቶችን የሚጨምር ይሆናል፡፡

**44. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ቀድሞ በመቋቋሚያ ደንብ የተቋቋሙ የልማት ድርጅቶች በዚህ አዋጅ እንደተቋቋሙ የሚወሰዱ ሆኖ መብትና ግዴታቸው የሚቀጥል ይሆናል፡፡

**45. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስፈልግ ደንብ የክልሉ የአስፈጻሚ አካላት ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ባለስልጣኑ አዋጁንም ሆነ ደንቡን ለማስፈፀም

**46. Jeefishshu Hee'rannonsa Seerubba**

Konni Lallawinni hanqanfantinokki hajubba aana daddalunna fitaabeerete seerubbara jeefishshu hee'rannonsa.

**47. Jeefishshu Hee'rannonsakki Seerubba**

Konni Lallawi ledo kiphamanno ayee lallawi, wodho, biddissi woy rosichi konni Lallawira worroonni hajubba lainohunni jeefishshu dihee'rannosi.

**48. Lallawu Loosu Aana Hosanno Yanna**

Kuni Lallawi Badheessa 12/2015 M.D hanafe loosu aana hosanno.

**Hawaasa, Badheessa 12/2015 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi**

**Mootimma Pirezidanticha**

የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**46. ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሕጎች**

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የንግድና የፍትሐብሔር ሕጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**47. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**48. አዋጁ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፤ መጋቢት ፲፪ ቀን ፳፻፲፭**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**